www.abyssinialaw.com




| 10ኛ አመት ቁጥር 51<br>10th Year No 51 | ባህር ዳር ግንቦት 25 ቀን 1997 ዓ.ም<br>Bahir Dar 2nd June 2005 |
|---|---|


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
## IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| የአንዱ ዋጋ ብር 2.00 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |
|---|---|---|---|


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 34/1997 ዓ.ም | Regulation No. 34/2005 |
| የአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ማደራጃ አዋጅ ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Urban and Rural Drinking Water Supply and Sewerage Services Organizing Proclamation Executive, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 34/1997 ዓ.ም.

የአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች እንደገና ማደራጃ አዋጅን ለማስፈፀም በክልል መስተዳድር ምክር ቤት የወጣ ደንብ

## REGULATION NO. 34/2005

A REGULAION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE IMPLEMENTATION OF THE PROCLAMATION RE-ORGANIZING THE URBAN AND RURAL DRINKING WATER SUPPLY AND SEWERAGE SERVICES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

www.abyssinialaw.com



የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ለክልሉ ነዋሪ ህብረተሰብ ጥራቱን የጠበቀ ንጽህ የመጠጥ ውሃ በበቂ መጠንና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማቅረብና የተቀላጠፈ የፍሣሽ ማስወገድ አገልግሎት ለመስጠት ይችሉ ዘንድ እንደገና የተደራጁበት አዋጅ ቁጥር 82/1995 ዓ.ም. የወጣ በመሆኑ፤

አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች አስፈፃሚው አካል ወደፊት እንደሚያወጣ በአዋጁ አንቀጽ 34 ስር አስቀድሞ የተደነገገ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በከተማና ገጠር የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 82/1995 አንቀጽ 34 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ማደራጃ አዋጅ ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 34/1997 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

1. "ደምበኛ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት ከከተማና ከገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት የንጹህ መጠጥ ውሃ ወይም የሣኒቴሽን አገልግሎት የሚያገኝ ሰው ነው::
2. "አዋጅ" ማለት የከተማና የገጠር መጠጥ

Whereas, proclamation No. 82/2003 to provide for the re-organization of the Urban and Rural drinking Water Supply and Sewerage Services has been issued for the purpose of enabling them to supply the inhabitants of the regional state with adequate and reliably clean drinking water and to render expeditious sewerage services thereof;

Whereas, it has been stipulated in advance under Art. 34 of the proclamation that the executive organ would, in some future time, issue a regulation necessary for the implementation of same;

Now, therefore, the council of the Amhara Regional Government, by virtue of the powers vested in it under the provisions of Art. 58 sub.Art.7 of the revised regional constitution and Art.34 of the Urban and Rural drinking Water Supply and Sewerage Services re-organization proclamation No. 82/2003, hereby issues this regulation:

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This regulation may be cited as the "Urban and Rural Drinking Water Supply and Sewerage Services" Re-organization Proclamation Executive, Council of the Regional Government Regulation No. 34/2005".

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "Client" means any person who receives safe drinking water supply or sanitary services from an urban and rural drinking Water Supply and Sewerage Service.
2. "Proclamation" means proclamation No.

www.abyssinialaw.com



ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶችን በአዲስ መልክ ለማደራጀት የወጣው አዋጅ ቁጥር 82/1995 ዓ.ም. ነው::

3. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ነው::

4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ክፍል ሁለት
## ስለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች አቅርቦትና አጠቃቀም

### 3. ስለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና የጥራት ደረጃ

1. ለከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲያቀርብ በአዋጁና በዚህ ደንብ ስልጣን የተሰጠው አካል የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ብቻ ነው:: ስለሆነም ልዩ ፍላጐቱ ታይቶ በቢሮው የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በክልሉ ከተሞች ውስጥ የውሃ መገኛ፣ ማጣሪያና ማከፋፈያ ተቋማትን መገንባትና ለራሱም ሆነ ለሌላ አካል የውሃ አገልግሎት ማቅረብ አይችልም::

2. ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያቀርበው የመጠጥ ውሃ የፌዴራሉ መንግስት የውሃ ሃብት ሚኒስቴር ያወጣውን የጥራት ደረጃ መመሪያ የጠበቀ ለመሆኑ በየወቅቱ ናሙና በመውሰድ ወይም በማስወሰድ በላቦራቱር ምርመራ የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል::

3. አገልግሎቱ በሚያቀርበው የመጠጥ ውሃ ላይ ማናቸውም ብክለት እንዳይደርስ የውሃ አቅርቦት ተቋማትንና አካባቢያቸውን ለብክለት ከሚያጋልጥ ንክኪ ነፃ በሆነ መንገድ መያዝና በሚያስተማምን ንፅህና መጠበቅ ይኖርበታል::

82/2003 promulgated to re-organize the Urban and Rural Drinking Water Supply and Sewerage Services.

3. "Bureau" means the Water Resource Development Bureau of the Amhara National Regional state.

4. "Person" means any natural or juridical body.

## PART TWO
## PROVISION AND UTILIZATION OF DRINKING WATER SUPPLY AND SEWERAGE SERVICES

### 3. Potable Water Supply and Quality Standard

1. The only organ authorized to provide safe drinking water to urban dwellers, in accordance with the proclamation and this regulation, shall be the urban drinking Water Supply and Sewerage Service. To that effect, unless specifically authorized to do so in consideration of his special interest by the Bureau, no person may be able to construct a water point as well as purification and distribution centers or to provide water service to himself or other bodies in any urban area of the regional state.

2. Any drinking Water Supply and Sewerage Service shall have the responsibility to regularly verify, through the laboratory test of a sample taken, as to whether the pot-able water it supplies for the user community, in accordance with sub-Art.1 of this article, that it meets the standards set in the guideline issued by the Federal Ministry of Water Resource.

3. The Service shall handle the water-supplying centers and their surroundings in such a manner that they are free from the touch of pollution-causing agents and thereby kept with reliable sanitation.

www.abyssinialaw.com



**4. የውሃ መጠንን ስለመቆጣጠር**

1. ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በዚህ ደንብ መሠረት የሚያቀርበውን የውሃ መጠን ለመቆጣጠር የሚያስችለው የውሃ ቆጣሪ መሣሪያ በደንበኞቹ የውሃ መስመር ላይ ይገጥማል::
2. አግባብ ካለው የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት የቅድሚያ እውቅናና ፈቃድ ውጪ በአንድ የውሃ መስመር ላይ የተገጠመን የውሃ ቆጣሪ መቀየር፣ እንዲቀየር ማድረግ፣ አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ እንዳይሰጥ ሆን ብሎ ማሰናከል ወይም ማበላሸት በዚህ ደንብ የተከለከለ አድራጐት ነው:: ዝርዝሩ ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ አገልግሎቱ በሚያወጣውና ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ ይገለፃል::

**4. Controlling Amount of Water**

1. Any drinking Water Supply and Sewerage-Service shall, in accordance with this regulation, install water-meter on water-spots of its clients so as to control the amount of water it provides with.
2. Changing or causing the change of the water-meter installed on water-spots without prior cognizance and approval of the relevant service and deliberately disrupting or damaging the smooth provision of the service are acts prohibited by this regulation. Details shall be provided for in a directive to be issued by the pertinent Service on the basis of this regulation and to be approved by its governing board.

**5. የውሃ ቆጣሪ ለደንበኛው ስለሚቀርብበት ሁኔታ**

1. ተገቢውን የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል የውሃ ቆጣሪን ለደንበኛው የሚያቀርበው ስለዚሁ ጉዳይ ጥያቄ የቀረበለት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ይሆናል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የተጠቀሰው አገልግሎት የተባለውን የውሃ ቆጣሪ በወቅቱ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ደንበኛው ጥራቱ በአገልግሎቱ አማካኝነት የተረጋገጠለትን የውሃ ቆጣሪ በራሱ ወጪ በግሉ ገዝቶ የማስገጠም መብቱ የተጠበቀ ይሆናል:: ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል::

**5. Provision of Water -Meter to Clients**

1. The one that provides water-meter to clients by charging proper service fee shall be any drinking Water Supply and Sewerage Service, to which the request regarding same has been submitted.
2. Notwithstanding the provisions sub-Art.1 of this article hereof, where the aforementioned Service is unable to provide with the said water meter on time, the client shall be entitled to buy the water-meter and have it installed with its quality having been approved by the service at his own expense. Details shall be determined by a directive.

**6. የውሃ ብክነትን ስለመከላከል**

1. ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት የውሃ ብክነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአፈፃፀም እቅድ በየአመቱ እያዘጋጀና ግብ እያስቀመጠ ለዚሁ ስኬታማነት የመስራት ኃላፊነት ይኖርበታል::

**6. Preventing Wastage of Water**

1. Any drinking Water Supply and Sewerage Service shall have the responsibility to prepare action plans and set goals on a yearly basis with the view to controlling the wastage of water and working for the success thereof.

www.abyssinialaw.com



2. ማንኛውም የውሃ አገልግሎት ደንበኛ በተዘረጋለት መስመር ላይ በቧንቧ ብልሽትም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ውሃ ሲፈስ ያጋጠመው እንደሆነ ወዲያውኑ አግባብ ላለው የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**7. የውሃ መገኛ ቦታዎችን ስለመከለል**

ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የውሃ መገኛ ቦታዎችን ከበካይ ነገሮች ለመከላከል ይቻል ዘንድ እንደነገሩ ሁኔታ በተወሰነ ርቀት በሁሉም አቅጣጫዎች እያንዳንዱን የውሃ መገኛ ሊከልል ይችላል፡፡ ከለላው የሚፈፀምበት ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**8. ስራዎችን በሌላ አካል ስለማስፈፀም**

ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንደውሃ ተቋማት ጥገና፣ በውሃ ማደያዎች ላይ የውሃ ሽያጭ፣ የቆጣሪ ንባብ፣ የውሃ ሂሣብ አሰባሰብ፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ ዲዛይኖችና ግንባታዎች ያሉትን ስራዎች ህጋዊ ፈቃድ ላላቸው ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በህግ መሠረት መስጠትና ማሰራት ይችላል፡፡

**9. ስለአገልግሎት ክፍያ**

ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከደንበኛው ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ የማስከፈል ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡ መመሪያው ክልል አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ለተገልጋዩ ህዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡

**10. ስለተከለከሉ ተግባራት**

ደምበኛው የሚከተሉትን ተግባራት እንዳይፈፅም በዚህ ደንብ ተከልክሏል

2. Any water service client shall, upon finding out leakage of water along the pipeline in his favor due to either damage or some other cause, have the responsibility to report same to the appropriate drinking water supply and sewerage service forthwith.

**7. Enclosing Water Points**

Any drinking Water Supply and Sewerage Service may, in consultation with the appropriate bodies, enclose a water point within the limit of a certain radius so as to protect the water from possible contamination thereof. Detailed implementation of such an enclosure shall be determined by a directive.

**8. Outsourcing of Activities**

Any Drinking Water Supply and Sewerage Service may, where it finds it essential, outsource by law such activities as the maintenance of water supply installations, water sale at distribution spots, water-meter reading, collection of water fees, a variety of studies, designing and construction of water-works and the like to be undertaken by other organizations licensed to render similar services.

**9. Service Fee**

Any drinking Water Supply and Sewerage Service shall have the power to exact a reasonable amount of fee from its clients for the service it provides in accordance with this regulation. Details shall be determined by a directive to be issued and circulated through a region wide Gazette.

**10. Prohibited Activities**

The client is prohibited, by this regulation, not to perform the following activities:

www.abyssinialaw.com



ሀ. ያለአገልግሎቱ የቅድሚያ እውቅናና ፈቃድ የተዘረጋለትን የውሃ መስመር ለሌላ ሰው አሣልፎ መስጠት ወይም ከዚሁ መስመር ላይ ሌላ ሰው ቀጥሎ በውሃው እንዲጠቀም ማድረግ፣

ለ. የሚቀርብለትን ንፁህ የመጠጥ ውሃ ከጓሮ አትክልቶች ማጠጫነትና ማስዋቢያነት አልፎ ለመደበኛ መስኖ ልማት እንዲውል ማድረግ::

## 11. የውሃ መስመሮችን ስለማጋራት

ደምበኛው ወጪውን ችሎ በተዘረጋለት በማናቸውም የውሃ መስመር ላይ ሌላ ደንበኛ ለመጠቀም ሲያመለክት አግባብ ያለው የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጥያቄ የቀረበበት መስመር ከአንድ በላይ ለሆኑ ደንበኞች በቂ ውሃ የማጋራት አቅም ያለው መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ አዲሱ ደንበኛ የመስመሩን ጠቅላላ ዋጋ አስቀድሞ ለከፍለውና መስመሩን ላስገባው የቀድሞው ደንበኛ ድርሻውን እንዲከፍል በማድረግ መስመሩን ሊያጋራው ይችላል::

## 12. ስለአገልግሎት አሰጣጥ ግልፅነት

የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ስራ አመራር ቦርድ በዚህ ደንብ መሰረት የሚሰጥ ማናቸውም አገልግሎት ለደንበኞቹ ግልፅነት የተሞላበትና በቅልጥፍና የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ያወጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል::

## 13. የፍሣሽ ማስወገድ አገልግሎት ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. ማንኛውም የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በተናጥል ወይም አግባብ ካላቸው ሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር በተቋቋመበት ከተማ ክልል ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት የፍሣሽ ማስወገድ አገልግሎት ሊያቀርብ ይችላል::

a. Transferring one's pipeline to another person or allowing same to be utilized by an extension without prior cognizance and approval of the Service;

b. Employing the safe, pot-able water provided hereof for the purpose of normal irrigation development, apart from using it to water horticultural seedinglings and beautify gardens.

## 11. Sharing Pipelines

Where a new client applies for utilization of a pipeline already laid at the expense of another original client and where the pertinent drinking Water Supply and Sewerage Service, whom the latter has approached for same, verifies that the line desired for use has got the capacity to supply adequate water for more than one clients, the new client may be made to share the line after having in advance paid the total coast and thereby refunded the former client to the extent of his own portion.

## 12. Transparency of Service Delivery

The managing Board of the drinking Water Supply and Sewerage Service shall set a standard enabling to insure the complete transparency and expeditiousness of the service to be delivered pursuant to this regulation for its clients as well as monitor the implementation thereof.

## 13. Sewage Disposal Service How Provided

1. Any urban drinking Water Supply and Sewerage Service may provide, in accordance with this regulation, separately or in collaboration with other government organs concerned, a sewage disposal service within the limit of the urban center of its establishment.

www.abyssinialaw.com



2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ህጋዊ ፈቃድ ያላቸውን የግል አገልግሎት ሰጪዎች እንቅስቃሴ በፍሣሽ ማስወገድ ስራ ከመሰማራት የማገድ ውጤት አይኖረውም::
3. በየትኛውም ከተማ ውስጥ የፍሣሽ ማስወገድ አገልግሎት የሚቀርበው ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ይሆናል:: የክፍያው መጠን አግባብ ያለው የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

14. የፍሣሽ አወጋገድ ስለሚፈፀምበት ሁኔታ

1. በየትኛውም ከተማ ውስጥ በፍሣሽ መቀበያና ማስተላለፊያ ቧንቧዎች፣ በዩች፣ ካናሎች ወይም የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች የሚሰበሰብ፣ የሚተላለፍ ወይም የሚጓጓዝ ማናቸውም ፍሣሽ የአካባቢን የተፈጥሮ ሃብት በማይበክልበትና የህብረተሰቡን ጤንነትና የአካባቢን ፅዳት በማይጐዳበት ሁኔታ መወገድ ይኖርበታል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የሚካሄደው ፍሣሽ የማስወገድ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ አካባቢም ሆነ በህዝብ ጤንነት ላይ ለሚያደርሰው ማናቸውም ጉዳት አገልግሎቱ ወይም ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው የድርጅት ባለቤት በወንጀልና በፍትሐብሄር ረገድ ተጠያቂ ይሆናል::

15. የመጠጥ ውሃና የፍሣሽ ማስተላለፊያ መስመሮችን ስለመዘርጋት

1. በከተማ ክልል ውስጥ የሚዘረጉ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ ማስተላለፊያ መስመሮች የከተማውን መሪ ዕቅድ ተከትለው መዘርጋት ይኖርባቸዋል:: ስለሆነም እነዚህን መስመሮች የመዘርጋት እቅድ ያለው ማናቸውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጉዳዩ የሚመለከተውን የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

2. The provision of sub-Art. 1 of this article may not have a prohibitive effect against those licensed private service-providers operating thereto.
3. Sewage disposal service in any urban center shall be provided by exacting a reasonable charge. The amount of the charge shall be determined by a directive to be issued by the pertinent drinking water supply and sewerage service with the view to implementing this regulation.

**14. Implementation of Sewage Disposal**

1. Any sewage captured, transmitted or transported by a capturing structure, sewer or transporting vehicles, as appropriate shall be disposed in such a way that it may not contaminate the natural resources of the environment or adversely affect the health and sanitation of the community as well as the surroundings.
2. The Service or owner of the enterprise licensed for the purpose shall be liable to criminal and civil actions for any damage it has caused to public health and the environmental resource while disposing sewage pursuant to the provision of sub-Art. 1 of this article hereof.

**15. Laying Potable Water and Sewage Transmission Lines**

1. Drinking water supply and sewage transmission lines in an urban center shall be laid in compliance with the requirements indicated in the master plane of same. To this end, any drinking water supply and sewerage service wishing to lay these lines shall, in advance, consult the city services' office or the

www.abyssinialaw.com



ወይም ማዘጋጃ ቤት በቅድሚያ ማግኘት ይኖርበታል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚዘረጋ የመጠጥ ውሃም ሆነ የፍሣሽ ማስተላለፊያ ቧንቧ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር ሣይቀበር በመሬት ላይ መዘርጋት የለበትም::
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የትራፊክ እንቅስቃሴ ጉልቶ በሚታይበት በማናቸውም አካባቢ የሚዘረጉ የመጠጥ ውሃና የፍሣሽ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች በተገቢው ጥልቀት በመሬት ውስጥ መቀበር ይኖርባቸዋል::

municipality.

2. The drinking water supply or sewage transmission pipeline to be laid, pursuant to sub-art.1 of this article hereof, may not be laid unburied on the surface of the ground, save cases attributable to forcemajeure.
3. Without prejudice to the provision of sub-Art.2 of this article hereof, drinking water supply and sewage transmission pipelines to be laid at any place largely exposed for heavy traffic activity shall be buried deeply enough beneath the ground.

### 16. የመጠጥ ውሃ ብክለትን ስለመከላከል

የመጠጥ ውሃ በፍሣሽ ቆሻሻ እንዳይበከል የውሃ መስመሮች ከፍሣሽ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች፣ በዩችና ካናሎች በጐንም ሆነ በከፍታ በቂ እርቀት ኖሯቸው ይዘረጋሉ::

### 16. Averting Contamination of Potable Water

Drinking water supply pipelines shall have a desirable distance from any sewage transmission pipes, tubes and channels, horizontally or vertically, with the view to preventing the pot-able water from possible contamination.

### 17. በቁፋሮ ስለሚደርሱ ጉዳቶች

ማንኛውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ ማስተላለፊያ መስመሮችን ለመዘርጋት በቁፋሮ ስራ ምክንያት በመንገዶች ላይ ለሚያደርሰው ማናቸውም ጉዳት ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ወይም የተበላሸውን መንገድ በነበረበት ሁኔታ መልሶ የመገንባት ኃላፊነት ይኖርበታል::

### 17. Damage Caused Due to Digging

Any drinking Water Supply and Sewerage Service shall be liable to pay compensation equivalent to the harm done or have the responsibility to reconstruct the road it has damaged whilst digging the ground in order to install pot-able water and sewage transmission pipes.

### 18. ስለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ መስመሮች ደህንነት

በዚህ ደንብ መሠረት የተዘረጉትን የመጠጥ ውሃና የፍሣሽ ማስተላለፊያ መስመሮች ወይም ሌሎች ተዛማች ስራዎች ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት የሰበረ፣ የቆረጠ፣ ያበላሸ ወይም ሌላ ማናቸውንም አይነት ጉዳት ያደረሰባቸው ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል::

### 18. Safety of Potable Water and Sewage Lines

Whosoever intentionally or by negligence breaks, disrupts, spoils or causes any other obstruction with regard to potable water and sewage transmission lines or other related works installed shall be liable to criminal laws.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሶስት
## ስለከተማና ገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ደረጃና አወቃቀር

**19. ዝርዝር መስፈርቶችና አፈፃፀማቸው**

1. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝር መስፈርቶች መሠረት በማድረግ በደረጃ ይፈረጃሉ፡-
   ሀ. አማካይ አመታዊ ገቢ ----------- 20%
   ለ. አማካይ አመታዊ ወጪ ----------10%
   ሐ. በባንክ ወይም በካዝና የሚገኝ የጥሬ ገንዘብ መጠን -------------------- 8%
   መ. አማካይ አመታዊ ከወጪ ቀሪ ገንዘብ --------------------------- 5%
   ሠ. በአመቱ የተሸጠ አማካይ የውሃ ምርት መጠን ------------------ 15%
   ረ. የሠራተኞች ብዛት --------------- 5%
   ሰ. ተቋማዊ ሁኔታ --------------------16%
   ሸ. የታሪፍ መጠን /ዝቅተኝነት/ ----- 3%
   ቀ. ስራዎች በመደበኛ ፕሮጀክት የመታቀፋቸው ወይም የፕሮጀክት ሰነድ የተዘጋጀላቸው መሆን አለመሆኑ -------------------- 3%
   በ. የሃይል ምንጭ --------------------- 2%
   ተ. የተገልጋይ ህዝብ ብዛት ----------10%
   ቸ. የሚመለከተው ከተማ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ------------------------------- 3%
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ስር ከተዘረዘሩት መስፈርቶች አኳያ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት ከተሞች መካከል ከፍ ያለውን መለኪያ ያገኘው የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ለመስፈርቱ የተሰጠውን የመቶኛ ክብደት ያገኛል።

## PART THREE
## CLASSIFICATION AND ORGANIZATION OF URBAN AND RURAL DRINKING WATER SUPPLY AND SEWERAGE SERVICES

**19. Specific Criteria and Their Application**

1. Without prejudice to the provision of Art. 5 sub-art 1 of the proclamation, urban drinking Water Supply and Sewerage Services existing in the regional state shall be classified by means of categorization on the basis of the specific criteria indicated herebelow:
   a. Average annual income --------------- 20%
   b. Average annual expenditure --------- 10%
   c. Amount of cash either in the bank or in coffer ------ 8%
   d. Average annual balance ---------------- 5%
   e. Average amount of water produced and sold per year-----------------------15%
   f. Number of employees ------------------ 5%
   g. Institutional status ---------------------16%
   h. Tariff size or its lowest limit -----------3%
   i. The fact as to whether or not activities are embraced by normal projects or whose project documents are prepared------ 3%
   j. Source of energy ---------------------2%
   k. Number of clients --------------------- 10%
   l. political and economic significance of the urban center------------ 3%
2. The drinking water supply and sewerage service which is ranked top in the classification of all the other services throughout the regional state against the criteria specified under sub-art 1 of this article shall be made to gain the weight of the percentage due to its qualification thereof.

www.abyssinialaw.com



3. የእነዚህ መስፈርቶች ዝቅተኛ መለኪያ ያላቸው ቀሪዎቹ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች በተነፃፃሪ ከከፍተኛው ክብደት ጋር እየተሰላና በተዋረድ ዝቅ እያለ የሚሄድ የመቶኛ ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡

3. The rest of the drinking Water supply and Sewerage Services having scored lower points as per these criteria, shall be given their respective values expressed in percentages hierarchically depending on as calculated against the highest weight thereof.

**20. ደረጃዎችን ስለመወሰን**

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተመለከቱት መስፈርቶች አጠቃላይ ድምር ውጤት መሠረት በክልሉ ከተሞች የሚገኙት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ደረጃ ከዚህ በታች በተመለከተው አኳኋን ይወሰናል:-

   ሀ. ውጤቱ ከ65% በላይ የሆነ-----1ኛ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት

   ለ. ውጤቱ ከ30% እስከ 64% የሆነ---2ኛ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት

   ሐ. ውጤቱ ከ15% እስከ 29% የሆነ---3ኛ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽአገልግሎት

   መ. ውጤቱ ከ10% እስከ 14%የሆነ----4ኛ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት

   ሠ. ውጤቱ ከ6% እስከ9% የሆነ --5ኛ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት

   ረ. ውጤቱ ከ6% በታች የሆነ ---የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት

2. ቢሮው በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች እና እያንዳንዱ አገልግሎት ያገኘውን የመለኪያዎች አጠቃላይ መቶኛ ክብደት ከሶስት እስከ አምስት አመት ባለው ጊዜ ውስጥ እያስጠና በሚደርስበት ግኝት መሠረት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶችን ደረጃ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

**20. Determination of Categories**

1. The hierarchy of drinking water supply and sewerage services located in the urban centers of the regional state shall, on the basis of the overall result of the criteria specified under Art. 19 sub-Art.1 of this regulation hereof, be determined as follows herebelow:
   a. Drinking water supply and sewerage service, whose result is above 65% ----- 1st class;
   b. Drinking water supply and sewerage service, whose result is from 30 % through 64% --- 2nd class;
   c. Drinking water supply and sewerage service, whose result is from 15 % through 29% --- 3rd class;
   d. Drinking water supply and sewerage service, whose result is from 10 % through 14% --- 4th class;
   e. Drinking water supply and sewerage service, whose result is from 6 % through 9% --- 5th class;
   f. That whose result is below 6% --- petty urban center drinking water supply and sewerage service.
2. The bureau may, from time to time, revise the classification of the dinking Water Supply and Sewerage Services in accordance with the findings reached upon studies conducted from 3-5 years depending on the criteria indicated under Art.19 of this regulation hereof and the points each Service has scored out of the total weight of the measurements expressed in percentage.

www.abyssinialaw.com



## 21. መረጃ ስለመስጠት

1. እያንዳንዱ የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ለደረጃ አወሣሰን የሚረዱ መረጃዎችን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በየአመቱ ለቢሮው ያቀርባል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰውን መረጃ በወቅቱ ያላቀረበ ማናቸውም የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በቢሮው የሚሰጠው የደረጃ ማሻሻያ ውሣኔ ተጠቃሚ አይሆንም::

## 22. አደረጃጀት

1. ቢሮው ለእያንዳንዱ ደረጃ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት መነሻ የሚሆን የስራ መዋቅር አዘጋጅቶ ሊያስተላልፍ ይችላል::
2. እያንዳንዱ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎትም የተላለፈለትን መነሻ የስራ መዋቅር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አሻሽሎ ወይም ባለበት ሁኔታ ቦርዱ ተጠሪ ለሆነለት አካል አቅርቦ በማስፀደቅ በስራ ላይ ሊያውለው ይችላል::

## 23. የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ተዋጽኦና ቁጥር ስለመወሰን

1. በአዋጁ አንቀጽ 6 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ እና አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሠረት በከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች አደረጃጀት ውስጥ የሚቋቋመው የሥራ አመራር ቦርድ ከ5-7 የሚደርሱ አባላት የሚኖሩት ሲሆን የአባላቱ ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል::
   - 1.1 በማዘጋጃ ቤት ከተሞች ውስጥ የተቋቋሙ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ቦርድ ተዋጽኦ፣
     - ሀ. በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ መሠረት ቦርዱ ተጠሪ በሆነለት አካል የሚሰየም ሰው -----

## 21. Provision of Information

1. Every Urban drinking Water Supply and Sewerage Service shall annually submit to the bureau any information with supportive documents helpful for the determination of classification thereof.
2. Any drinking water supply and sewerage service-failing to proved information stipulated under sub-Art.1 of this article hereof may not enjoy the benefits emanating from the class-determining decision to be granted by the bureau.

## 22. Organization

1. The Bureau may prepare and convey down a proposed structure pertaining to each drinking Water Supply and Sewerage Service with every class to be used as a starting modal.
2. Every drinking Water Supply and Sewerage Service may, on its part, apply the proposed structure referred to it either as it appears or with the necessary amendments, should that be so required, upon the approval of the organ, to which the board is accountable thereof.

## 23. Determination of Composition and Number of the Managing Board Members

1. The Managing Board to be established within the Organization of the urban drinking Water Supply and Sewerage Services pursuant to the provisions of Art.6. letter No (a) and Art.7 sub-Art.2 of the proclamation, shall comprise 5 through 7 members, whose composition is listed as follows:
   - 1.1 composition of the board of the drinking water supply and sewerage services to be constituted in municipal cities;
     - a. one designated by the organ, to which the board remains accountable pursuant to the provision of Art. 7 sub-Art. (4)

www.abyssinialaw.com



---------------- ሰብሣቢ፣

ለ. የሚመለከተው ከተማ ማዘጋጃ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ተወካይ -------------------- አባል፣

ሐ. ከተማው በታቀፈበት ወረዳ አደረጃጀት ውስጥ የሚገኘው የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የውሃ ቡድን መሪ ------- አባል፣

መ. የዚሁ ወረዳ የጤና ዴስክ ኃላፊ ወይም ተወካይ ----------- አባል፣

ሠ. የገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ---------- አባል፣

ረ. ከመካከላቸው አንዷ ሴት መሆኗ ሣይቀር ከውሃ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ የሚመረጡ ሁለት ተወካዩች --------------- አባላት፣

ሰ. የከተማው መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ----------------------------- አባልና ፀኃፊ

1.2 በከተማ አስተዳደሮች ሥር የተቋቋሙ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ቦርድ ተዋጽኦ፣

ሀ. በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ መሠረት ቦርዱ ተጠሪ በሆነለት አካል የሚሰየም ሰው --------------------- ሰብሣቢ፣

ለ. የከተማ ነክ አገልግሎቶች ስራ አስኪያጅ ----------------- አባል፣

ሐ. የከተማው አስተዳደር የጤና ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ይህ በሌለበት ሁኔታ የከተማው አስተዳደር የተማከለበት ዞን ጤና ዴስክ ኃላፊ ወይም ተወካይ -------------------- አባል፣

መ. የከተማው አስተዳደር፣የገንዘብና

of the proclamation ……. Chairperson;

b. Managing head or representative of the municipal city concerned ………………………….. member:

c. water team leader affiliated to the office of Agriculture and Rural Development located within the woreda organization, wherein the city is held …………. member:

d. Managing head or representative of the Health Desk in this same woreda ......................... member;

e. Managing head or representative of the Finance and Plane Office ………… member;

f. With one of them being female, two representatives selected from among the water-user community ………………… members;

g. Managing head of the urban of the urban drinking Water Supply and Sewerage Service concerned. .....................member and Secretary.

1.2 Composition of the board of the drinking Water Supply and Sewerage Services to be established under urban administrations:

a. One designated by the organ, to which the board remains accountable, pursuant to the provision of Art. 7 sub Art 4 of the proclamation....... chair person.

b. Managing head of the city-related services.......... member.

c. Managing head or representative of the health office in the urban administration, or in the farmer's absence, the head of the health desk of the zone, in which the urban administration is accommodated....... ..............member.

d. Managing head of the Finance and Plan

www.abyssinialaw.com



ፕላን ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ይህ በሌለበት ሁኔታ ከተማው የተማከለበት ዞን ገንዘብና ፕላን ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ --------------------------------- አባል፣

ሠ. ከመካከላቸው አንዷ ሴት መሆኗ ሳይቀር ከውሃ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ የሚመረጡ ሁለት ተወካዬች ------------------------------ - አባላት፣

ረ. የከተማው መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ----------- --------------- አባልና ፀኃፊ::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በባህርዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ የክልሉ ውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ተወካይ እንዲሁም በሌሎች የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ከተማው የሚገኝበት ዞን ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የውሃ ስራዎች ጉዳይ ኃላፊ እንደአግባብነታቸው የየቦርዶቹ ተጨማሪ አባላት ሆነው ያገለግላሉ::

Office of the city administration, or in the farmer's absence, head or representative of the Finance and Plan Office of the zone, wherein the urban center is accommodated....................member;

e. With one of them being female, two representatives selected from among the water user community.........members.

f. Managing head of the urban drinking water supply and sewerage service concerned.........member and secretary

2. Without prejudice to the provision of sub-Art. 1 of this Article hereof a representative from the Regional Water Resource Development Bureau in the Bahir Dar city Administration and the head of Water Works' Affairs in the zonal office of Agriculture and Rural development, wherein the urban Administration is located, in the rest of urban centers shall, as may be appropriate, serve in the capacity of Additional board members.

**24. ከውሃ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ስለሚመረጡ ወኪሎች የአገልግሎት ዘመን**

በዚህ ደንብ መሠረት ከውሃ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ተመርጠው በቦርድ አባልነት የሚሰየሙት ወኪሎች የአገልግሎት ዘመን 3 አመት ይሆናል:: ሆኖም ይህ ድንጋጌ ለሁለተኛ የአገልግሎት ዘመን ከመመረጥና ከማገልገል የሚያግዳቸው አይሆንም::

**24. Tenure of Representatives Elected from Among the Water-User Community**

The tenure of those representatives of the water-user community elected and designated, in accordance with this regulation, as members of the board, shall be three years; provided, however, that this provision may not prohibit same from being re-elected and serve for the second term.

**25. ስለአበል ክፍያ**

የቦርድ አባላት መጠኑ በተጠሪው አካል ወደፊት የሚወሰን አበል ሊከፈላቸው ይችላል::

**25. Payment of Allowance**

Members of the board may be paid an allowance, the amount of which is to be determined by the body supervising the board.

www.abyssinialaw.com



**26. ተጠያቂነት**

የቦርድ አባላት በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ካለመወጣታቸው የተነሣ በአገልግሎቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የግልና የጋራ ተጠያቂነት አለባቸው::

**27. ስለሥራ አመራር ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ አባላት ጥንቅርና የአገልግሎት ዘመን**

1. የአዋጁ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት በክልሉ ውስጥ በሚገኝ በእያንዳንዱ የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ደረጃ የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ ይደራጃል::
2. ኮሚቴው ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል::
3. የኮሚቴው አባላት ከሚከተሉት የተውጣጡ ይሆናሉ:-
   ሀ. የከተማው ሥራ አመራር ተወካይ፣
   ለ. ከተማው የታቀፈበት ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የውሃ ቡድን መሪ፣
   ሐ. ከተማው የታቀፈበት ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ
   መ. ከተማው የታቀፈበት ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ
   ሠ. ከውሃ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ውስጥ ለ3 አመታት የአገልግሎት ዘመን ተመርጠው የሚሰየሙ ሁለት ተወካዬች
   ረ. የንዑስ ከተማው መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ::
4. ኮሚቴው የራሱን ሰብሣቢ መርጦ የሚሰይም ሲሆን የንዑስ ከተማው መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ በፀኃፊነት ጭምር ያገለግላል::

**26. Accountability**

Members of the board shall individually and collectivity be liable for the damage sustained to the service on account of their failure to discharge their responsibilities in accordance with this regulation and the proclamation.

**27. Tenure and Membership Composition of the Management Support-Providing Committee**

1. A management support-providing committee shall be organized at the level of each and every petty urban center drinking water supply and sewerage service found in the regional state, pursuant to the stipulations under Art.22 sub-Art.1 of the proclamation.
2. The Committee shall consist of members numbering from five through seven
3. Membership of the committee shall be drawn from the following:
   a. A management representative of the urban center,
   b. water team leader in the office of the Agriculture and Rural Development of the woreda, wherein the urban center is incorporated,
   c. head or representative of the Health Office of the woreda, wherein the urban center is incorporated,
   d. head or representative of Education Office of the woreda, wherein the urban center is incorporated;
   e. Two representatives to be elected from among the water-user community to render service for three years' term;
   f. Head of the petty urban center drinking water supply and sewerage service.
4. The committee shall elect and designate its own chairperson, whereas the head of the petty urban center drinking water supply and sewerage service shall serve as the secretary, as well.

www.abyssinialaw.com



**28. ስለጾታ ውክልና**

ከሥራ አመራር ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት ሴቶች መሆን ይኖርባቸዋል::

**29. የአስተዳደር አካላት ኃላፊነት**

በዚህ ደንብ መሠረት የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶችን የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴዎች የማስመረጥና የማደራጀቱ ኃላፊነት ከየአካባቢው የውሃ ቡድን ጋር በመተባበር አገልግሎቶቹ የሚገኙባቸው የወረዳና የቀበሌ አስተዳደሮች ኃላፊነት ይሆናል::

**30. ስለገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች አመራር**

1. የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች የሚመሩት በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የእያንዳንዱ ጣቢያ ተጠቃሚ ሕብረተሰብ በሚያቋቁማቸው የውሃ ኮሚቴዎች አማካኝነት ይሆናል::
2. የአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት እያንዳንዱ የውሃ ኮሚቴ ከ5-7 የሚደርሱ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴቶች መሆን አለባቸው::
3. ኮሚቴው የራሱን ሰብሣቢ ከአባላቱ መካከል በምርጫ ይሰይማል::

**31. ስለኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን**

የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን 3 ዓመት ይሆናል:: ሆኖም ማናቸውም አባል ከታመነበት ለዳግመኛ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጥ ይችላል::

**28. Gender Representation**

More than one-third of the members of the management support-providing committee shall have to be women.

**29. Responsibilities of Administrative Bodies**

The task of having the management support providing committees belonging to the petty urban center drinking water supply and sewerage services elected and organized in accordance with this regulation shall, in cooperation with the water teams of the respective localities, be the responsibility of those Woreda and Kebele Administrations, wherein the services are located.

**30. Management of The Rural Drinking Water Supply and Sewerage Stations**

1. Rural drinking water supply and sewerage Stations shall be managed by the water committees to be established on the part of the water user-community benefiting from each and every station as per the proclamation and this regulation.
2. Each water committee shall, pursuant to what is provided under Art.27 sub-Art 1 of the proclamation, have members numbering from 5 through 7, more than half of whom must be women.
3. The committee shall designate its own chairperson by election from among the membership.

**31. Tenure of the Committee Members**

The tenure of the Committee members shall last three years; provided, however, that any one of them may be eligible for re-election to serve for the second term.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**32. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

**33. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የዚህ ደንብ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

**34. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ-ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ግንቦት 25 ቀን 1997 ዓ.ም.
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

## PART FOUR
## MISCELANEOUS PROVISONS

**32. Inapplicable Laws**

Any law, directive or customary practice contrary with this regulation may not apply to matters provided for therein

**33. Power to Issue Directives**

Without prejudice to the various provisions hereof, the Bureau may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

**34. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional state.

Done at Bahir Dar
This 2nd day of June 2005
Yosef Retta
Head of Government of
the Amhara National Regional State